# ትግራዋይ ከፅንፈኞች እንዴት ይታረቅ?

ያፌት ዓምደ (04/17/09)
Yaf_et@yahoo.com

ይህን ፅሑፍ እንድፅፍ ያነሳሱኝ ነገሮች በርከት ያሉ ቢሆኑም ከነዚህ ውስጥ ካናዳ የሚኖረው "እናታቸው የሞተችባቸው እና ገበያ የሄደችባቸው እኩል ያለቅሳሉ" ፣የግርማ ካሣ መቀለ የሁላችን ናት፣ ለግርማ መልስ ተብሎ በአርዮን የተሰጠ አስተያየት እና በዋርካ "ጉግል"፣ "ዱራሰንበት"… በሚል ስም በመግባት ሃሳባቸው የሚያቀርቡ እና የመሳሰሉት ፅሑፎች በማንበቤ ነው:: በዚህ መሰረት የሚከተለው አስተያየት አቀርባለው:: ይህንን ስፅፍ የማንም ፖለቲካ ፓርቲ አባል እንዳልሆንኩኝ እና ሀሳቤ ብቻ እንደፃፍኩኝ እንድትረዱልኝ እጠይቃለው:: የአማርኛ ግድፈት ካለው አስተካክላቹ እንድታነቡት በትህትና እጠይቃለው::

## <u>የትግራይ ሰው ምን አጠፋ?</u>

ሁላችንም እንደምናውቀው ለኢትዮጵያዊነት መነሻ የሆነው፣ የኢትዮጵያዊነት ሚስጢርና ምንጭ የሆነቺው አክሱም በኢትዮጵያ ሰሜናዊ ክፍል በአሁኑ ትግራይ ክልል የምትገኝ ሲሆን የዚህ ስልጣኔ መነሻም የዚህ አካባቢ ሰዎች መሆናቸው ይታወቃል:: ከዚህ በመነሳት ኢትዮጵያዊነት ያለ ትግራዋይነት ትርጉም የማይሰጥ ሆኖ ሲያበቃ ከትግራዎት በላይ እኛ ነን ኢትዮጵዊያን የሚሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ያሉበትና ከዚህም በላይ በአሁኑ ሰዓት ትግራዎት ኢትዮጵዊያን አይደሉም የሚሉ ግለሰቦች የተፈጠሩበት ግዜ ደርሰናል::

በኢትዮጵያ ገዢዎች ታሪክ አንድ መንግስት ወደ ስልጣን ሲወጣ ለስልጣኑ መጠናከር ይረዳው ዘንድ ስልጣን ላይ የሚያስቀምጣቸው የመንግስትን ዓላማ ተግባራዊ የሚያደርጉና የራሱ ሰዎች መሆናቸው የግድ ይላል:: ይህ የሚሆንበት በአገራችን ስር የሠደደ የተጠናከረ የመንግስት መዋቅርና በህግ ብቻ የሚያምን ተቋም አለመኖሩ ነው የሚል ግምት አለኝ ::

ይህን ከላይ ያስቀመጥኩት እውነታ ታዲያ በትግራይ ተወላጆች ላይ ገኖ የሚታይበት በሌሎች ላይ (ለምሳሌ በአማራ) ግን ምክንያታዊ ለማድረግ የሚደረገው ጥረት እንዴት ነው? አንድ አንዳቸው የትግራይ ህዝብ ቢበዛ "20" ሠዎች ብቻ (በስልጣን ላይ ያሉትን ማለቴ ነው) ፣ ሁሉም አንድ አይነት አስተሳሰብ አንድ አይነት ውሳኔ የሚወስን አድርገው የሚቆጥሩ አይታጡም:: ሁኖም የትግራይ ተወላጆች እንደሌላው ህዝብ ሁሉ በእውነት ላይ አንድ አይነት አስተሳሰብ (ምክንያቱም እውነት አንድ ነች እና) በውሸት ላይ ግን የሚለያይ ህዝብ ነው::

በስልጣን ላይ የሚገኙ የትግራይ ተወላጆች እንደሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ ከትግራይ ህዝብም የሚደግፋቸው እና የሚቋወማቸው እንዳለ አሌ የማይባል ሐቅ ሆኖ ሳለ የትግራይ ተወላጅ ስለሆኑ ብቻ ኢህአዴግ ነው የሚለው አባባል ተገቢ አይመስለኝም:: የብዙዎች ጥያቄ የኢህአዴግ ደጋፊ ካልሆነ ለምን እኛ ከምናደርገው "ትግል"ጋር አይቀላቀልም የሚል ነው:: ይህንን እንዳይሆን ከሚያደርጉት አንዱ የአላማ መለያየት ነው::

## <u>የአላማ ልዩነቶች</u>

የትግራይ ህዝብ ለህወሓት/ኢህአዴግ እንደ ጠላት አያየውም:: ጠላት አይደለም ማለት ግን ሁሉም ይደግፈዋል ማለት አይደለም:: ህወሓት/ኢህአዴግ የገባቸው ቃሎች ካልፈፀመ ለሌላ እድል መስጠት ይችላል:: የገባው ቃል የሚፈፅም ከሆነ ደግሞ ሌላ አያስፈልገውም:: ከሌሎች "ኢትዮጵያዊያን" በተለይ "አክራሪው/ፅንፈኛው ዲያስፖራ" ጋር ያለው ልዩነቶች:-

1. *ኢተዮጵያ በቀኝ ገዢዎች እየተገዛች ነው ብሎ አያምንም*:: ከአብራኩ የወጡትን ልጆች ቀኝ ገዢዎች ናቸው ብለው ከሚከሡ ጋር አብሮ መስራት እንዴት ይቻላል? አብዛኞቹ የኢህአዴግ ተቃዋሚዎች ኢህአዴግን አገር ያፈራችው ለአገር 'የማይጠቅም" ድርጅት ነው ብለው እንኳ ማመን እማይፈልጉ ብዙዎች ናቸው

::የሚበዙት ኢትዮጵያዊ አይደለም እያሉ ነው የሚቀሰቅሱት:: መቀለ “የትግሬ እንጂ የኢትዮጵያ አይደለችም” የሚሉም ቀላል አይደሉም:: የትግራይ ህዝብ ‘ወያኔ ከአገራችን ይውጣልን’ ከሚሉ ጋር ሲታገል እስኪ ያሳያቹ?

2. *የትግራይ ህዝብ ከሌላው ህዝብ በላይ ተጠቅመናል ብሎ አያምንም:: በአንፃሩ አልተጠቀምንም ብሎ የሚያስብ ነው::* ቅድም የገለፅኩት እናታቸው ገበያ የሄደችባቸው እና እናታቸው የሞተችባቸው እኩል ያለቅሳሉ ብሎ የፃፈ ወገን በኔ አስተሳሰብ ልክ አይደለም:: እናቱ የሞተችበት አንዴ አልቅሶ ይወጣለታል :: እንደማትመለስ ልቡ ስለሚያውቅ ተስፋ የለውም ደግሞ ደጋግም የማልቀሱ ሁኔታም አይኖርም :: ተስፋ ያለው ግን ቢያንስ እናቱ እስከምትመጣ ድረስ ማልቀሱ አያቆምም ምክንያቱም ትመጣ ይሆናል የሚለው ነገር በልቡ አለና :: በኔ እምነት ማልቀስ ያለበት እናቱ ገበያ የሄደችበት ነው:: የትግራይ ህዝብም ለ ኢህአዴግ ‘እንደጠበቁት አላደረክልኝም’ ብሎ ቢጠይቅ ሀጥያት የለዉም:: መሰራት አይችልም ብሎ ቢያምን ግን መጠየቅ አየሰፈልግም ነበር:: የካናዳው ሰውየ አይመስልህም? (በዩኒቨርስቲ ቆይታህ ነበሩ ላልካችው ልዩነቶች(Discrimination) እኔም የጠቀስከው ግዜ ባች ስለሆንኩኝ በቀጣይ መልስ ለመስጠት እመኩራለው)

የትግራይ ህዝብ የተታገለበት ዋናው አላማ በኢትዮጵያ የነበረው ጨቋኝ ስርአት አስወግዶ በእኩልነት ላይ የተመሰረተች ኢትዮጵያ መፍጠር ነው:: ይህ ስል የትግራይ ህዝብ ብቻ ነው ለዚህ አላማ የተታገለው የሚል እምነት የለኝም:: ይህንን ዓላማው ግቡን እንደታሰበው መተዋል አልልም:: ሁኖም የትግራይ ህዝብ አሁን ያለው ሁኔታ በደርግና በአፄው ግዜ ከነበረው ሁኔታ በብዙ ዕጥፍ ይሻላል:: እኔ አሁን ኢህአዴግና ደርግ የሚወዳደሩበት ሁኔታ እንደሌለ ነው እማምነው:: ኢህአዴግ ከግዜ ወደ ግዜ የተሻለ ነገር እየሰራ ነው ወይ የሚለው ነው ዋናው ጥያቄ:: ከዚህ በላይ መስራት የሚችል ሌላ ድርጅት አይኖርም ወይ የሚለው ነው መወያያ መሆን ያለበት:: ይህንን ከሰብአዊ መብት ጥሰት፣ ከመልካም አስተዳደርና ከልማት ጋር አያይዘን ልናየው ይገባል:: የትግራይ ህዝብ በደርግ ግዜ ይሻለው ነበር ካልኩኝ ግን ‘ውሸታም’ የሚለው ቃል አይገልፀኝም::

3 *የጠላቴ ጠላት ወዳጄ የሚባለው አባባል ቦታ የለውም::* ከሚመሳሰልህ ጋር አብሮ መስራት ወሳኝ መሆኑን በጣም ከማመናችን የተነሳ የመደራጀት ቃል በሰፊው ስንጠቀምበት እንስተዋላለን:: ይሁን እንጂ ይህንን የሚሆነው አንተን  ከሚመስልና በተለይ የአላማ አንድነት  ወሳኝ ነገር ነው::(የክበበው ገዳ ገብረ መድህን የሚለውን ይመልከቱ፡ ቂቂቂ)

በ1997 ዓ.ም. አቶ ገብሩ አስራት በአዲስ አበባ በተደረገው የተቃውሞ ስልፍ ተገኝቶ የተናገረው ነገር ምን ያህል የትግራይ ህዝብን እንዳሳዘነ እና ይሠጠው የነበረው ክብር እንዳወረደ ራሱን በመጠየቅ መልሱን ማግኘት ይቻላል:: በቅርቡ ሸገር አዲስ 102.1 በተሰኘው FM ሬድዮ አርቲስት እያሱ በርሀ ስለ እነ አቶ ስየ አብርሃ ተጠይቆ የሰጠው ምላሽ *“እነ አቶ ስየ አሁን ስልጣን ላይ ካሉት አልለያቸውም እኩል ነው እማከብራቸው ነገር ግን እነ ስየ ከነዶ/ር መራራ እና ዶ/ር በየነ ጋር እንሰራለን ሲሉ አልገጥምልህ አለኝ”* ነበር ያለው:: ዶ/ር  ሃይሉ አርአያ እና ስየ አብርሃ አብረው ሲሰሩ እስኪ እግዚሄር ያሳያችሁ:: ስየ የህዝብ ጥያቄ ምን እንደሆነ ጠንቅቆ የሚያውቅ ጀግና እና ዶ/ር ሃይሉ በደርግ ግዜ እንኳን የትግራይን ህዝብ እሮሮ ማዳመጥ ያቃታቸው የ“ትግራይ” ሰው::

## አቶ ገብሩ እና አቶ ስየስ ለምን?

አቶ ገብሩ እና አቶ ስየ ለኛ ለኢትዮጵያ ህዝብ ያደረጉት አስተዋፅኦ ያለኝን አክብሮት ልገልፅ እወዳለው:: ህወሐት ውስጥ ባጋጠመ የሀሳብ ልዩነት ከፓርቲው በመገለላቸው በመጥፎ አጋጣሚው አዝናለው:: ከፓርቲው እንዲወጡ የተወሰነው ውሳኔ ግን እደግፈዋለሁ:: ምክንያቱም ሁለት የማይሰማሙ አካላት አብረው መስራት የለባቸውም:: ይህንን ሃሳብ እነ ገብሩም የሚቃወሙት አይመስለኝም:: በህወሐት ታሪክ ውሰጥ እንደዚህ ዓይነት ክስተቶች ሲያጋጥሙ ተመሳሳይ እርምጃ ሲወሰድ አብረው ወስነዋል እና ነው(የ1969 እና የ1977ዓ/ም የነበረው ሁኔታ ተጠቃሽ ነው)::

አሁን ወዳለው ሁኔታ ስንመጣ ግን ግራ የሚያጋባ ነው:: አቶ ገብሩ በሊቀመንበርነት የሚመሩት ዓረና ትግራይ ባወጣው ፕሮግራም ላይ እወክለው

አለው ለሚለው የትግራይ ህዝብ የሚገልፅ ነገር ምንም አላየሁም:: በአሁኑ ሰአት የአሰብን ጉዳይ የትግራይ ህዝብ ጥያቄ አይደለም:: የባህር በር ስለማንፈልግና ጥቅሙ ስለማይገባን ሳይሆን የኢትዮጵያ እንዳልሆነ ቀድሞ በህወሐት(እነ ገብሩን ጨምሮ) ትምህርት ስለተሰጠንና እዉነታው ስላመንበትም ጭምር ነው:: ታድያ አሁን ምን ተገልፆላቸው ይሆን ይህንን ጥያቄ የሚያቀርቡት:: እሺ ሀሳባቸው የመቀየር መብታቸው እንኳን ብንቀበል በህዝብ ፊት ሁለት ተቃራኒ ሀሳቦች እንዴት በአንድ ሰው ማስተላለፍ ይቻላል?

ይህ ብቻ አይደለም በቅርቡ በአዲስ ነገር ጋዜጣ 2ኛ ዓመት ቁጥር 073 መጋቢት 05 ቀን 2001 እትም ላይ "የትምህርት ዘርፉን ገድሎ ማልቀሱ ይቁም!" በገብሩ አስራት እንዲሁም በዚሁ ጋዜጣ 2ኛ ዓመት ቁጥር 072 የካቲት 28 ቀን 2001 እትም ላይ "የትምህርት ነገር" በስየ አብርሃ የቀረቡት አስተያየቶች ሳነብ በጣም ነው ያዘንኩባቸው:: የትምህርት ዘርፉ ላይ የጥራት ችግር እንዳለው ሁላችን የምንስማማበት ጉዳይ ነው:: እነ አቶ ገብሩ ግን እንደዚህ ብሎ የመናገር የሞራል ብቃት የላቸዉም:: የትምህርት ፖሊሲው ሲወጣ እነሱም አጃቸው አስገብተዋል:: አቶ ገብሩ የትግራይ ፕሬዚዳንት በነበረበት ግዜ ያለውን የትምህርት ፖሊሲ ባስተዋወቀበት ወቅት "ከአሁን በኋላ የተማረ ገበሬ ነው የምንፈልገው...ስምንተኛ ክፍል የወደቀ አይደግምም ገበሬ ይሆናል...." ብሎ ነበር:: በዚህ ምክንያት በትግራይ ህዘብ ምን ዓይነት ተቃዉሞ እንደደረሰው የምያስታዉሰው ይመስለኛል:: ታድያ የትምህርት ነገር መች ነው እንዴ እንደሞተ የሚገባው? ጅብ በማያዉቁት አገር ሂዶ... ነገር ይሆን?

## ማጠቃለያ

ይህንን ፅሑፍ የፃፍኩት ለማንም ለማስደሰትም ሆነ ለማስቀየም አይደለም:: በተለያዩ ጋዜጦችም ሆነ ዌብ ሳይቶች የትግራይ ተወላጆችንና ትግራይን በሚመለከት የሚፃፉት ሃሳቦች በጣም ስለሚያሳዝነኝ ነው:: እኛ እንደማንኛዉም

የኢትዮጵያ ህዝቦች የሰብአዊ መብት ጥሰት፣ የመልካም አስተዳደር እጦት እና የልማት ችግሮች ያሉብን ቢሆንም  የደላን ተንደላቀን የምንኖር ከሌላው ኢትዮጵያዊ ወገኖቻችን በተለየ ጥቅም የምናገኝ አስመስሎ ለማቅረብ የሚደረግ ሙከራ ሊታረም የሚገባው ስህተት ነው እላለው::

የትግራይ ህዝብ ተቃዋሚዎች የሚደግፋቸዉም ሆነ የሚቃወማቸው እንደምትገምቱት ዘራቸው በመቁጠር አይደለም:: ከላይ እንዳስቀመጥኩት አቶ ገብሩ ትግራዋይ መሆኑን ከማንም በላይ አውቃለው:: አሁን እያነሳቸው ባሉት ሃሳቦች ግን አልስማማም:: የትግራይ ህዝብ የማህበራዊ፣ የኢኮኖሚ እና የፖለቲካ ጥያቄዎች አሉት:: እነዚህን ለይቶ ማዉጣት ያስፈልጋል:: ለምሳሌ አንድ ቁስል ያለበት ዉሻ ቤት ውስጥ ገብቶ አልወጣ ሲል እንደምንም አርገን በእንጨት/በበትር ቁስሉን ብንነካው በርግጎ እንደሚወጣ ይታወቃል:: ይህንን ወደኛ ስንመልሰው የኔ ችግሮች ለይቶ እፈታልህ አለው ለሚለኝ ሰው ያልተገደበ ድጋፍ እሰጠው አለው:: የኔ ጥያቄ የማያሳስበው እኔን መጠቀምያ ብቻ ሊያደርገኝ ለሚሞክር ግን እኔም ግድ የለኝም::

የዓላማ አንድነት መፍጠር መጀመርያ መሰራት ያለበት ጉዳይ ነው::  የሚነሱ ጥያቄዎች የግለሰብ ፍላጎት ለማርካት ከሚሆን ይልቅ የህዝብን ፍላጎት የሚያንፀባርቅ ቢሆን ተቀባይነቱ የሰፋ ይሆናል:: በሌሎች ተቀባይነት ለማግኘት ሲባል ብቻ እወክለው አለው የምትለዉን የህብረተሰብ ክፍል ጥያቄ ችላ ማለት የስልጣን ጥማት እና ስግብግብነት የሚያሳይ ስለሆነ ከመጀመርያው ውክልናዎን ቢያስተካክሉ ይመረጣል:: የህዝብን የልብ ትርታ ማዳመጥ የቻለ ፖለቲከኛ እድለኛ ነው:: ምክንያቱም ሁሉም ከጎኑ ነው:: ፖለቲከኞቻችን እንደዚህ እንድትሆኑ እመኛለው:: .............

*ኢትዮጵያ ለዘልአለም ትኑር!!*